ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 37 መጋቢት15/2018 ዓ.ም

በውስጥ ገፆች

የጥቅም ግጭትን በተገቢው መንገድ ካልተቆጣጠርነው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ሊያበላሽ የሚችል ተግባር ነው - ክብርት ጥሩማር አማረ

ገጽ 2

ከ1 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ ያለደረሰኝ ሽያጭ የፈጸሙ 8 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ዋሉ

ገጽ 3

በቱርክ በኤርዶጋን ተቀናቃኝ እና በሌሎች 400 ሰዎች ላይ የሙስና ችሎት ተጀመረ

ገጽ 4

በኢትዮጵያ የሙስና ወንጀል ምርመራ ጥራትና ተገቢነትን ማላቅ የሚያስችል ተግባር በጥምረት ለማከናወን ኮሚሽኖቹ ከስምምነት ደረሱ

በግምገማ መድረኩ የተገኙት የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ) ኮሚሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት ከዜጎች የሚቀርቡ የሙስና ወንጀል መረጃዎችን በማመንጨት ተገቢው የሙስና ወንጀል ምርመራ እንዲካሄድባቸው በማድረግ የግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሁም ውጤታማነትን ማዕከል ያደረጉ ስራዎች እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡እንደሀገር የሙስና ወንጀል መረጃ ቅበላ፣ ምርመራ፣ ክስና ክርክር፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ በሙስና ወንጀል የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ እና የማስተዳደር ሂደት በላቀ የሙያ ሥነምግባርና ብቃት በግልጽ እንዲከናወኑ በማድረግ ተገማች እና ወጥነት ያለው የሙስና ወንጀል ህግ ማበከበር ሥርዓተን ማረጋገጥ ያበፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል በበኩላቸው ሁለቱ ኮሚሽኖች በጥምረት መስራት ሙሰኞችን በመረጃና ማስረጃ በማጋለጥ ተጠያቂ እንዲሆኑ በዚህም ሁለቱ ኮሚሽኖች፣ የፍትህና የዳኝነት ተቋማት በቅንጅት መረጃና ማስረጃን መሰረት በማድረግ ሙሰኞችን ተጠያቂ የማድረግ ስራን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል፡፡ከማድረጉም በተጨማሪ የሙስና ወንጀል ምርመራ መዝገብ ዝግጅት ላይ የሚስተዋሉ የህግ ክፍተቶችን በመለየት የሙስና ወንጀልን መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡የሙስና ወንጀል በተናጠል ወይም በአንድ ተቋም ብቻ ከመከላከል በጥምረት መስራት ውጤታማ እንደሚያደርግ ጠቁመው፣ ለዚህም በመንግስት በኩል ያለው ቁርጠኝነት የቅንጅት ስራን የተሳካ እንደሚያደርገው እና ለውጥ መር ትግል ሊደረግ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ክቡር ኮሚሽነር ጀነራል አክለውም በበጀት አመቱ 6 ወራት ውስጥ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ተጠርጣሪዎች በህግ ጥላ ስር ሆነው ምርመራ እየተካሄደባቸው መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው በበኩላቸው ኮሚሽኑ የማስተማር፣ የመከላከል እና ህግ የማስከበር ስራዎችን ከፍትህ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራቱ ውጤታማ ያደርገዋል ብለዋል፡፡ሁለቱ ኮሚሽኖች ከዚህ በፊት በሙስና ወንጀል ምርመራ በትብብር ለመስራት የሥራ መግባቢያ ሰነድ በተፈራረሙት መሠረት የእስካሁኑ ጉዞ እና የቀጣይ የጋራ ሥራን በላቀ ተነሳሽነት እና ቁርጠኝነት ለማከናወን በቴክኒክ ኮሚቴ የታገዘ ተጨባጭ ሥራዎች ለመስራት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

አገርዓቀፍ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና የቀጣይ ሶስት አመታት ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት ላይ ግምገማዊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

አገርዓቀፍ የትስስር ጉባኤው ባለፉት ሶስት አመታት በሥነምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል፣ በተቋማዊ ማስፈጸም አቅም ግንባታ ጋር በተያያዘ ለፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥና ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የጋራ ስምምነት በመፍጠር የተቀናጀ ዘርፍ ተኮር የፀረ-ሙስና ትግል በውጤታማነት ተግባራዊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡በጉባኤው የ2016-2018 በጀት ዓመት የመካከለኛ ዘመን የልማትና የኢንቨስትመንት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና የቀጣይ ሶስት ዓመታት ስትራቴጂክ እቅድ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡በትስስር ጉባኤው ባለፉት ሶስት ዓመታት የተከናወኑ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎች፣ በአፈጻጸም የታዩ ጠካራ ጎኖችና ክፍተቶችእንዲሁም የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ የጋራ መግባባት ተፈጥሯል፡፡በቀጣይ ሶስት ዓመታትም በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣ ሙስናን አስቀድሞ መከላከል፣ የፀረ-ሙስና ትብብር እና በተቋም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራ ተመላክቷል፡፡ በትስስር ጉባኤው የፌደራል፣ የክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮች፣ ም/ኮሚሽነሮች እና የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ተሳትፈዋል፡፡

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

የጥቅም ግጭትን በተገቢው መንገድ ካልተቆጣጠርነው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ሊያበላሽ የሚችል ተግባር ነው - ክብርት ጥሩማር አማረ

የጥቅም ግጭት በሁሉም ተቋማት የሚከሰት በመሆኑ በተገቢው መንገድ ካልተቆጣጠርነው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ሊያበላሽና የሕዝብ አመኔታን ሊያሳጣ የሚችል ተግባር ነው ሲሉ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ድኤታ ክብርት ወ/ሮ ጥሩማር አማረ ተናግረዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ይህንየተናገሩትየፕላንና ልማት ዘርፍ ከፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለዘርፉ ከፍተኛ አመራሮች “ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር” በሚል ርዕስ በተዘጋጀው የሥልጠና መድረክ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ነው።ሚኒስትር ዴኤታዋ አክለውም የመንግሥት ተቋማት ተልዕኳቸውን በታማኝነት፣ በግልጽነት እና በተጠያቂነት ለማከናወን ሥነ-ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን መከተል አለባቸው ብለዋል። በተለይ የፕላንና ልማት ዘርፍ ለሀገር ዕድገት ወሳኝ ከሆኑ ተቋማት አንዱ እንደመሆኑ መጠን፣ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት ሥነ-ምግባርን የተላበሰ አመራርና ከጥቅም ግጭት የጸዳ የውሳኔ አሰጣጥ መርህ ሊኖረው ይገባል።

ዘርፉ ዕቅድ ማቀድ ብቻ ሳይሆን፣ ዕቅዶች በተገቢው መንገድ መፈጸማቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበትም ገልጸዋል።

ሙስናን በዘላቂነት ለመቀነስ በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ አበክሮ በመሥራት፣ ቀደም ሲል ያጣናቸውን የሥነ-ምግባር እሴቶች እንደገና መገንባት ይኖርብናል።

“ዛሬ ላይ ዋጋ እያስከፈሉን ያሉት ትናንት በትውልድ ላይ ያልሠራናቸው ሥራዎች ናቸው” ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በአገልግሎት አሰጣጥ የማኅበረሰቡን የእርካታ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ከጥቅም ግጭት የጸዱ፣ ተገቢና ምክንያታዊ ውሳኔዎችን መወሰን እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል።

የሥልጠናው ዋና ዓላማም እያንዳንዱ አመራር የነበሩበትን ክፍተቶች ለይቶ መፍትሔ ማበጀት እንዲችል ግንዛቤ መፍጠር መሆኑንም ተናግረዋል።

በመጨረሻም ሥልጠናው በተቋሙ የግልጽነትና የተጠያቂነት ባህል እንዲጎለብት ትልቅ ዕውቀት የሚፈጥር በመሆኑ፣ የተገኘውን ልምድና ተሞክሮ እስከታችኛው መዋቅር ላሉ ሠራተኞች ማውረድ እንደሚገባ አሳስበዋል። ተጠሪ ተቋማትም እንደየሥራ ባህሪያቸው የሥልጠና ዕቅድ በማዘጋጀት ሥልጠናውን መስጠት እንዳለባቸውና

የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችም ይህን ተልዕኮ ወስደው እንዲፈጽሙ አቅጣጫ ሰጥተዋል።የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው፤ ሙስናን መቀነስ የሚቻለው የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ሲቻል ብቻ እንደሆነ ገልጸዋል። “ትልቁ ችግር የአመለካከት መዛነፍና የማኅበራዊ እሴቶች መሸርሸር ነው” ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ የአመለካከት ችግር ያለባቸውን ደፍሮ መናገር ባለመቻላችንና ያለመሰልቸት ባለማስተማራችን አሁን ላይ ለብዙ ችግሮች እየተጋለጥን እንገኛለን ብለዋል።እንደ ኮሚሽን ሦስት የፀረ-ሙስና ስትራቴጂዎችን እንከተላለን ያሉት ኮሚሽነሩ፤ እነዚህም የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ፣ ሙስናን አስቀድሞ መከላከልና ሕግ ማስከበር

መሆናቸውን አስረድተዋል። የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ ዘርፍ ተኮር ሥልጠናዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ሲሆን፣ የሥልጠና ሞጁሎቹም የዘርፎቹን የጥናት ግኝት መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው።

በተለይ ከፍተኛ አመራሩ ላይ ትኩረት የተደረገው፣ አመራሩ ትግሉን በግንባር ቀደምነት ካልመራው ውጤት ስለማይመጣና በዕለት ተዕለት ሥራው ሊገጥሙ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን አስቀድሞ ለመከላከል ግንዛቤው ወሳኝ ነው ብለዋል።የፀረ-ሙስና ትግሉን ለመምራት ቅንጅታዊ አሠራር እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት ም/ኮሚሽነሩ፤ አመራሩ ሙስናን አምርሮ የሚታገል ከሆነ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉን እንደ ቀኝ እጁ ማየት ይኖርበታል።

ለዚህም የሥነ-ምግባር መከታተያ፣ የሕግ፣ የለውጥና የኦዲት የሥራ ክፍሎች ተናበው መሥራት አለባቸው፤ ለዚህም የአመራሩ ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን አሳስበዋል።

የሥልጠናው ተሳታፊዎች በበኩላቸው ሥልጠናው ወቅታዊና አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፣ የጥቅም ግጭት በሀገር ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስቀድሞ ለመከላከል ትልቅ ግንዛቤ እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል። በተለይ ውሳኔዎችን በጥንቃቄ በማየት ፍትሐዊና ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት ሦስቱን የሥነ-ምግባር እሳቤዎች ማለትም፡ ሕግ ተኮር (Deontology)፣ ውጤት ተኮር (Consequentialism) እና ሥብዕና ተኮር (Virtue ethics) መመልከት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘባቸውን ገልጸዋል።

ከ1 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ ያለደረሰኝ ሽያጭ የፈጸሙ 8 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ዋሉ

በወለል ምንጣፍ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው ከ1 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ ያለደረሰኝ ሽያጭ ሲፈጽሙ የተገኙ 8 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የግብር ስወራን ለመከላከልና የንግድ ሥርዓቱን ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ የተጠናና ድንገተኛ ኦፕሬሽን በዛሬው ዕለት አካሂዷል፡፡

በዚህም በ7 የምንጣፍ ንግድ ድርጅቶች ውስጥ ደረሰኝ ሳይቆርጡ ሽያጭ ሲፈጽሙ የተገኙ 8 ተጠርጣሪዎች በሕግ ቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡ ድንገተኛ የኦፕሬሽን ሥራውን ቢሮው ከአዲስ አበባ ፖሊስ ጋር በመቀናጀት ማከናወኑን ገልጿል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ የመንግሥትን ጥቅም ለማሳጣት ከታክስ አስተዳደር አዋጅ በተፃረረ መልኩ ያለደረሰኝ ሽያጭ በመፈፀም ወንጀል ተጠርጥረው ጉዳያቸው በፖሊስ ተይዞ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ይሆናል፡፡ በቀጣይ ቀናትም የኦፕሬሽን ተግባሩ በሌሎች ዘርፎች ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተመላክቷል፡፡

ባለፉት ሁለት ወራት ብቻ በጎማ፣ በኤሌክትሮኒክስና በኮንስትራክሽ፣ በስጋ ቤት፣ በግንባታ ዕቃዎች እንዲሁም በሱፍ ልብስ ንግድ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች በድምሩ 74 ተጠርጣሪዎች ያለደረሰኝ ሽያጭ ሲፈፅሙ እጅ ከፍንጅ ተይዘው በሕግ ቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡ በምርመራ ኦዲት ዳግም ተጠያቂ መሆናቸውም የሚታወስ መሆኑን ገልጾ የከተማው ገቢዎች ቢሮ በፌስቡክ ገጹ አመላክቷል፡፡

ኮሚሽኑ በአለም ባንክ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ለማረጋገጥ (verification) ስራ ለሚሰማሩ ሰራተኞች ኦረንቴሽን ሰጠ

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደ ሀገር በአለም ባንክ ፕሮጀክት የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዱ ስለመሆናቸው በየሁለት ዓመቱ የማረጋገጥ ስራ (verification) በማከናወን ለአለም ባንክ ሪፖርት እየላከ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያውን ዙር የማረጋገጥ ስራን ፕሮጀክቶቹ በሚተገበሩባቸው ተቋማት ለሚሰሩ ባለሙያዎችን ኦረንቴሽን ተሰጥቷል፡፡ በኦረንቴሽኑ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የፀረ-ሙስና ህጎችና አለም አቀፍ ስምምነቶች አፈጻጸም ማስተባበሪያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሃረጎት አብርሃ ኮሚሽኑ ይህን የማጣራት (verification) ስራ በዓመት ሁለት ጊዜ በማከናወንና መረጃ በመሰብሰብ የተጣራ ሪፖርት ለአለም ባንክ ይልካል ብለዋል፡፡ አሁን የምናካሂደው ማጣራት የ2018 የመጀመሪያው ዙር ስራችን ነው፡፡ ስራው ከሀገራዊ ፋዳው በዘለለ አለም አቀፋዊ አንድምታ ያለው መሆኑን በመረዳት በትልቅ ሀላፊነትና ተነሳሽነት ማከናወን ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እያንዳንዱን ኬዝ በጥንቃቄ በማየት በአስተማማኝ መረጃና ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት ማቅረብ ከእያንዳንዱ ቡድን እንደሚጠበቅ ገለፀው፣ ስራውን ለማከናን ምን ዓይነት መረጃ፣ የመረጃ ምንጮች እና

መረጃውን እንዴት እንሰበስባለን የሚለውን በማጤን በተረጋጋ መንፈስ ማጣራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ለስራው የተመደበውን ጊዜ በአግባቡ በመጠቅም ሪፖርት በወቅቱ ለስራ ክፍሉ ማቅረብ እንደሚጠበቅም አሳስበዋል፡፡

ከሙስና እና ማጭበርበር የፀዳ (corruption and fraud free) የፕሮጀክት አፈጻጸም እንዲኖር የተሻለ ውጤት ካላቸው ሀገራት መካከል ሀገራችን ኢትዮጵያ አንዷ ስለሆነች ልምዷን እንድታካፍል በአለም ባንክ ተመርጣ ለአምስት ሀገራት ልምዷን አካፍልለች ብለዋል፡፡

ኮሚሽኑ የአለም ባንክ ድጋፍ በሚያደርግባቸው በስድስት ፕሮጀክቶች ላይ የማረጋገጥ (verification) ስራ ያከናውናል ያሉት መሪ ስራ አስፈጻሚው፣ እንዚህም ፕሮጀክቶች በውሃ፣ በመብራት፣ በአየር ንብረት፣ በጤና፣ በመሰረተ-ልማትና በሰው ሀብት ላይ የሚተገበሩ ናቸው ብለዋል፡፡

የፀረ-ሙስና ህጎችና አለም አቀፍ ስምምነቶች አፈጻጸም ትብብርና ትስስር ማጎልበቻ ዴስክ ኃላፊ አቶ በለጠ ብርሀኑ በበኩላቸው በዚህ የማረጋገጥ ስራ እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል ብለዋል፡፡

አንደኛው ተግባር ፕሮጀክቶቹ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ተግባር ደግሞ ጥቆማ ቀርቦባቸው የተመዘገቡ ኬዞች ያሉበትን ደረጃ ማወቅ ማለትም በቀረቡ ኬዞች ላይ ችግሮቹ ሙሉ በሙሉ ስለመፈታታቸው ወይም በሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማረጋገት ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጁ የነበሩ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር አዋለ

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ሀሰተኛ የብር ኖት፣ ክብ ማህተምና ቲተሮች፣ የተለያዩ የግልና የመንግስት ትምህርት ማስረጃዎች፣ የተሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ፣ የቀበሌ መታወቂያዎችንና ሌሎች ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጁ የነበሩ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር አውሏል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ የአድማ መከላከል ፖሊስ መምሪያ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ጋር በጋራ በመቀናጀት በማህበረሰቡ ጥቆማ መሰረት የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጁ የነበሩ ሁለት ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን አስታውቋል፡፡

የአድማ መከላከል ፖሊስ መምሪያ ኦፕሬሽን ምክትል አዛዥር ኮማንደር ነፃነት ታደሰ እንደገለጹት፣ አቶ እዝራ ወይፍ እና አቶ አለልኝ አዲስ የተባሉ ግለሰቦች ሀሰተኛ ሰነዶችን ለማጭበርበር ተግባር ለመጠቀም ሲያዘጋጁ እንደነበር በማህበረሰቡ ጥቆማ መሰረት መያዛቸውን ተናግረዋል፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ሀና ማሪያም አካባቢ ላይ በተደረገው የጥምር ኦፕሬሽን የተለያዩ የመንግስትና የተቋም ስምና ማህተሞችንና ሌሎች ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጁ ከህብረተሰቡ በደረሰ ጥቆማ እጅ ከፍንጅ መያዛቸው ተገልጿል፡፡

ፖሊስ ባከናወነው ፍተሻ ሀሰተኛ የብር ኖት፣ ክብ ማህተምና ቲተሮች፣ የተለያዩ የግልና የመንግስት ትምርት ማስረጃዎች፣ የተሽከርካሪ መንጃ ፈቃድና የቀበሌ መታወቂያዎችን እንዲሁም መሰል ሀሰተኛ ሰነዶችም በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ህብረተሰቡ ማናቸውንም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲመለከት ሰው አልባ ፖሊስ ጣቢያ፣ በህብረተሰብ ተሳትፎ መተግበሪያ፣ በነፃ የስልክ መስመር 991 እንዲሁም በአቅራቢያው ለሚገኙ የፀጥታ አካላት ቀርቦ ጥቆማ መስጠቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አስተላልፏል፡፡

የኮልፌ ቀራንዮ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ተገልጋዮችን ለእንግልት ያደረጉ 12 ባለሙያዎችን እርምጃ ወሰደ

የኮልፌ ቀራንዮ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ላልተገባ ጥቅም ተገልጋዮችን ለእንግልት የዳረጉ 12 ባለሙያዎች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰዱን ገልጧል፡፡ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ በክፍለ ከተማው ለሚገኙ 3,216 አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጆች የይዞታ ልኬት ስራ አጠናቆ መብት እንዲፈጠርላቸው ለማፅከል መላኩን አሳውቋል፡፡

የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ከህብረተሰቡ የሚነሱ የአገልግሎት መዘግየት ቅሬታዎችን ለመፍታት ባለፉት ሁለት ዓመታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አገልግሎት አሰጣጡን የማዘመን ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

በዚህም በርካታ አገልግሎቶችን ከእጅ ንክኪ በማላቀቅ ተገልጋዮች ባሉበት ቦታ ሆነው ቀልጣፋና ፍትሃዊ መስተንግዶ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም ተሻሽሎ በተዘጋጀው ሲስተም የቅሬታና አቤቱታ መቀበያን ጨምሮ 14 ሞጁሎችን በማዘጋጀት የተገልጋዮችን እርካታ ይበልጥ ለማሳደግ ጥረት አድርጓል፡፡ ይህ ሥርዓትም አጭር፣ ፈጣን እና ድግግሞሽን የሚያስቀር መሆኑ በተግባር የተረጋገጠ ውጤታማ ቴክኖሎጂ ነው፡፡

የኮልፌ ቀራንዮ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በተሻሻለው ሲስተም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እየተቻለ የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ተገልጋዮችን አጉላልተዋል ባላቸው 12 ባለሙያዎች ላይ ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዱን የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ኃላፊ ወ/ሮ ሳምራዊት በቀለ ገልጸዋል፡፡

ውሳኔ ለመስጠት በሚል ጉቦ በመቀበል የተጠረጠረች የፍርድ ቤት ዳኛ ተከሰሰች

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳሪክቶሬት ዐቃቤ ሕግ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ የሆነችውን ቴዎብስትያ ጌታቸው (የቀድሞ ስሟ ቃልኪዳን) ላይ የሙስና ወንጀል ክስ መሰረተ። ተከሳሿ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9 ንዑስ ቁጥር 1 (ሀ) እና ቁጥር (2) ስር የተመላከተውን ድንጋጌ መተላለፏን ጠቅሶ ዐቃቤ ሕግ ዝርዝር ክስ አቅርቧል።ተከሳሽ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 1ኛ የቤተሰብ ችሎት ዳኛ ሆና ስትሰራ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በስራ ኃላፊነቷ የተሰጣትን ሥልጣንና የተጣለባትን አደራ ወደ ጎን በመተው ውሳኔ ለመስጠት ጉቦ ጠይቃ የተቀበለችውን ገንዘብ እንዳስቀመጠች እጅ ከፍንጅ መያዟን በክሱ ዝርዝር ላይ ተገልጿል።በዚህ መሰረት ተከሳሿ የማይገባትን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በሁለት ተከራካሪ ግለሰቦች መካከል በችሎት በነበረው የባልና ሚስት ንብረት ክርክር ላይ አመልካች ንብረቱ በግሌ ያፈራሁት ነው በሚል ያቀረበችውን አቤቱታ ተጠሪ ያመነ በመሆኑ ክስ መስማት ሳያስፈልግ ውሳኔ ለመስጠት በየካቲት 26 ቀን 2018 ዓ.ም ቀጠሮ ይዛ እያለ፣ በቀጠሮ ቀን አመልካች በችሎት ስትቀርብ ተከሳሽ አመልካችን "የአንቺ ጉዳይ በቢሮ ነው የሚታየነው" በማለት በቢሮ እንድትቀርብ ማድረጓ በክሱ ላይ ተመላክቷል።

በዚህ መልኩ ተከሳሿ በቢሮ ባለጉዳይዋን እንድትቀርብ ካደረገች በኋላ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለማስጠት 600 ሺህ ብር እንድትከፍላት የጠየቀቻት እና አመልካችም ይህንን ያህል ገንዘብ የመክፈል አቅም እንደሌለት ስትገልጽላት 'እስበሽበት ነይ" በማለት በሚቀጥለው ቀን በቢሮ እንድትቀርብ የቀጠረቻት መሆኑ በክስ ዝርዝሩ ላይ ሰፍሯል። በዚህም አመልካች ጉዳዩን ባለቤቷ ለሆነው ግለሰብ በማሳወቋ ባለቤቷም ምንም አይነት ገንዘብ እንዳትከፍል በመምክር አመልካች በቀጠሮ ቀን በድጋሚ በቢሮ ስትቀርብ ተከሳሽ የጠየቅችውን ገንዘብ አመጣሽ ወይ ብላ በመጠየቅ አመልካችም ገንዘቡን መክፈል እንደማትችል በምትጠልጽበት ጊዜ ተከሳሽ ዳኛ በመጨረሻም 100 ሺህ ብር እንድትከፍል በመጠየቅና የተጠቀሰውን ገንዘብ ለመቀበል በመስማማት በየካቲት 30 ቀን 2018 ዓ.ም የግል ተበዳይ ገንዘቡን ይዛ ስትመጣ ውሳኔው እንደሚሰጣት መናገሯ ተጠቅሷል።

ከዚህም በኋላ አመልካችም አስቀድማ ለህግ አስከባሪ አካላት ባሳወቀችው መሰረት በመጋቢት 01 ቀን 2018 ዓ.ም የተጠየቀውን 100 ሺህ ብር ለተከሳሽ በቢሮዋ በመስጠት ተከሳሽም ገንዘቡን ተቀብላ ባስቀመጠችበት ቅጽበት እጅ ከፍንጅ የተያዘች መሆኑን በመጥቀስ፤ ተከሳሿ ያላትን የዳኝነት ስልጣን ያለአግባብ በመጠቀም ስልጣንን ያለአአግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ፈጽማለች ሲል ዐቃቤ ሕግ ክሱን አቅርቧል።በተጨማሪም በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 113 ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት በአማራጭነት ሌላኛውን ማለትም የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 11 ንዑስ ቁጥር (2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ጠቅሶ የወንጀል ድርጊቱን አካትቶ ዝርዝር ክስ አቅርቦባታል።

በቱርክ በኤርዶጋን ተቀናቃኝ እና በሌሎች 400 ሰዎች ላይ የሙስና ችሎት ተጀመረ

የኢስታንቡል ከንቲባ ኤክሬም ኢማሞግሉ ከ400 በላይ ከሚሆኑ ሌሎች ተከሳሾች ጋር ፍርድ ቤት ቀርበዋል።

ተከሳሾቹ በሰፊ የሙስና ወንጀል የተከሰሱ ሲሆን፤ ተቺዎች ግን ጉዳዩ በቱርክ ተቃዋሚዎች ላይ ያነጣጠረ ፖለቲካዊ እርምጃ ነው ብለዋል።

ለአንድ ዓመት ገደማ በእስር ላይ የሚገኙት ኢማሞግሉ፤ ለ23 ዓመታት ስልጣን ላይ የቆዩት የፕሬዝዳንት ረሲፕ ጣይብ ኤርዶጋን ዋነኛ ተቀናቃኝ ናቸው።

እርሳቸው በቁጥጥር ስር በዋሉ በጥቂት ቀናት ውስጥ በ2028 ለሚካሄደው ምርጫ የዋነኛው ተቃዋሚ ፓርቲ እጩ ሆነው ተመርጠው ነበር።

የችሎቱ ሂደት በውጥረት ውስጥ የጀመረ ሲሆን፤ ኢማሞግሉ የመናገር ዕድል እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም የዳኞች ቡድኑ ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል።

ከ402ቱ ተከሳሾች መካከል አብዛኞቹ፣ ኢማሞግሉ ከ2019 ጀምሮ በሚመሩት የኢስታንቡል ሜትሮፖሊታን ማዘጋጃ ቤት ውስጥ የሚሰሩ ናቸው።

ብዙዎቹ የሪፐብሊካን ሕዝባዊ ፓርቲ የተመረጡ ባለስልጣናት ሲሆኑ፤ ጋዜጠኞችም ከተከሳሾቹ መካከል ይገኙበታል።

ባለፈው ዓመት መጋቢት የኢማሞግሉ መታሰር፤ ላለፉት አሥር ዓመታት በቱርክ ያልታየ የጎዳና ላይ ተቃውሞዎች መካከል ትልቁን ለሳምንታት የቀጠለ ተቃውሞ ቀስቅሶ ነበር።

ኢማሞግሉ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ከባድ ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል።

መልካም ዜጋ

አንድ መልካም ዜጋ ለሀገሩ የሚከፍለው ዋጋ በገንዘብ ወይም በቁስ ብቻ የሚለካ ሳይሆን፣ በማንነቱና በዕለት ተዕለት ተግባሩ የሚገለጥ ጥልቅ ኃላፊነት ነው። ይህ የዜግነት ዋጋ በዋናነት በሚከተለው መልኩ ይገለጻል፡- ለዚህም ወድቆ የተገኘን የአንዲትን ግለሰብ ብር የመለሱት ፖሊሶች የመልካም ዜጋ ትልቅ ማሳያዎች ናቸው፡ነገሩ እንድህ ነው የጮርሶ ወረዳ ፖሊስ የአይን ቅኝት እያደረጉ በጮርሶ ከተማ ዉስጥ ለዉስጥ የእግር ጉዞ እያደረጉ 01 ቀበሌ መናሀሪያ መንደር ሲደርሱ አንድ ትንሽ የሴት እጅ ቦርሳ ያገኛሉ። ይህንን ቦርሳ ያገኙት ፖሊሶች ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ከፍተው ሲያዩ በዉስጡ ያለዉ

አራት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ አምስ ብር መሆኑን ያረጋግጣሉ።ከዚያም በኋላ ወድቆ የተገኘውን ንብረት ለማስመዝገብ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ላይ ሳሉ ገንዘቤ ጠፍቶብኛል አገኛችሁ የምትል አንድት ሴት ወ/ሮ ሰናይት ተሰማ የምትባል መጣች እንባዋን እያነባች ሰዎችን ትጠይቃለች፡ ፡ በመጨረሻም እጄ ንፁህ ልቤ ርህሩህና ታማኝ የህዝብ አገልጋይ የሆኑት ፖሊሶች ገንዘቧ ምንም ሳይጎልባት የአከባቢው የአንይን እማኞች ባሉበት በአደባባይ ቆጥረው ማስረከባቸውን የጮርሶ ወረዳ ፖሊስ ህዝብ ግንኙነት ዘግቧል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
EARS

ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS

ርዕሰ -አንቀፅ

የሙስና ስጋት ተጋላጭነትን ለመቀነስ ህጎች ከተጽዕኖ ነፃ ሆነው እንዲወጡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ክትትልና ቁጥጥር አስፈላጊ ነው!

የሙስና ሥጋት ተጋላጪነትን ለመቀነስ ህግ ሲወጣ ከሦስተኛ ወገን ነጻ ሆኖ የፓርላማ የህግ አወጣጥ ሂደትን ተከትሎ መውጣት ይኖርበታል። አንድ ህግ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ህግ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት ቋሚ ኮሚቴዎች ነጻና ገለልተኛ ሆነው ሂደቱን መከታተል እና በጥንቃቄ መመርመር ይኖርባቸዋል፡ ፡ ህግ ከማመንጨት ጀምሮ ህግ በማርቀቅ ሂደት ውስጥ የህግ ባለሙያዎችን፣ የህዝብንና የባለድርሻ አካላትን አስተያየት በማካተት ከጥቅም ግጭት የፀዳ፤ ለህዝብ የወገነ እና የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን መቀነስ የሚያስችል ህግ ማውጣት አስፈላጊ ነው።

እንደ ሀገር የሚወጡ ህጎች በህዝብ ተሳትፎና ግልጽ አሰራር ተከትለው የማይወጡ ከሆነ በአንዳ አንድ ተጽዕኖ ፈጣሪ አካላት ተጠምዝዘው ለሙስና ሥጋት መጋለጣቸው አይቀሬ ነው። በግለሰብ ወይም ቡድን ተጽዕኖ ውስጥ ሆኖ የሚወጣ ህግ ደግሞ የህዝብን ጥቅም ሊያስከብር አይችልም። የህግ ረቂቆች የግል ወይም የቡድን ፍላጎት የሚንፀባረቅባቸው ከሆነ ለጥቅም ግጭት የመጋለጥ እድላቸውም ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም ህግ በሚረቅበት ሰዓት የግል ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ አንዳንድ ግለሰቦች የተቋማት ሀላፊዎችን እጅ በመጠምዘዝ እነሱ በሚፈልጉት መልኩ ተቀርጾ ለህግ አውጭው አካል እንዲቀርብ ሊያደርጉ ይችላሉ። ስለሆነም የሚወጡ ህጎች የግል ወይም የቡድን ድብቅ ፍላጎት ማስፈጸሚያ መሳሪያ እንዳይሆኑ በጥንቃቄ የመመርመርና የመፈተሽ ሀገራዊ ሀላፊነት በቋሚ ኮሚቴዎች እጅ ላይ የወደቀ ነው። እያንዳንዱ የህግ አንቀፆች የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ተቃኝተው እና የህዝብን ጥቅም የሚያስከብሩ መሆናቸውን በህግ ባለሙያዎች ተገምግመው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

የህዝብ ተወከዮች ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ሂደቱን ከመከታተል በተጨማሪ ህጎች ከወጡ በኋላ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ በሚሆኑበት ወቅት ለሚፈጠሩ ክፍተቶች ተጠያቂነት እንዲኖር የሚፈቅዱ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ የአስፈጻሚው አካል በተቋማት ደረጃ በሚመነጩ የህግ ረቂቆች ላይ የተቋሙን ሰራተኞች እና አጋር አካላትን ያሳተፈ ግብዓት በማሰባሰብ ለቋሚ ኮሚቴዎች የማቅረብ እና ታማኝ መረጃ የመስጠት ሀላፊነት አለባቸው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የፓርላመንታሪ ሥርዓት ተከታይ እንደመሆኗ መጠን ነጻና ገለልተኛ የሆነ ህግ አውጭ ህግ አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚ የመንግስት አካለት እንዲኖር ህገ-መንግስቱ ይፈቅዳል። ስለሆነም የህዝብ እንደራሲዎች የወከሉትን ህዝብ ጥቅም እና ፍላጎት ማሟላት የሚችሉ ህጎች ማውጣት እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ጭምር መከታተል ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ህጎች ለሙስና ሥጋት ተጋላጭ እንዳይሆኑ በሶሥቱም የመንግስት አካላት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ውጤታማ መናበብ እና ሚዛናዊ (Effective check and balance) አሰራር መርህን ባከበረ መልኩ ሊሆን ይገባል።

ስለሆነም በሚወጡ ህጎች የምክርቤት አባላት ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ከማድረግ ጀምሮ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ መስራት ይኖርባቸዋል።

ቆይታ

የጥቅም ግጭት ለሙስና በር የሚከፍት በመሆኑ በጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሰጠቱ ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ በእጅጉ ይረዳል - ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ!

የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ ሀገራዊ የስነምግባር ግንባታ እና የፀረ-ሙስና ሥራዎችን በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ነው። ስለሆነም የኮሚሽኑ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ክፍል በየ15 ቀናት ውስጥ የተከናወኑ የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎችን በተለያዩ የጋዜጣዋ አምዶች ከፋፍሎ በማዘጋጀት "በዲጅታል ጋዜጣ' አማካኝነት ለህዝቡ ተደራሽ የማድረግ ስራ እየሰራ ይገኛል። በዚህም የኮሚሽኑ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ከመከላከያ ዘርፍ የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ የሥነ-ምግባር እና መልካም አስተዳደር መምሪያ ሀላፊ ከሆኑት ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ ጋር በሥነ-በምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል እና ማስተዳደር ዙሪያ አጭር ቆይታ አድርጋለች። በቆይታችን ወቅት የተነሱ ሀሳቦችን እነሆ።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በመጀመሪያ ለቃለ-መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አያመሰገንሁ፣ በመቀጠል ራስወን እና ሀላፊነትዎን ለአንባቢያን ያስተዋውቁ;

ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ፡- ስሜ ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ ይባላል በመከላከያ ዘርፍ የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ የሥነምግባርና መልካም አስተዳደር መምሪያ ሀላፊ ነኝ።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ለዘርፉ ከፍተኛ አመራሮች በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ዙሪያ ሥልጠና መሰጠቱ ሙስናን ከመከላከል አንፃር ሊኖረው የሚችለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ፡- በሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና በጥቅም ግጭት ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ለከፍተኛ አመራሩ ትልቅ ግንዛቤን የሚፈጥሩ ናቸው። እንደ አንድ ትልቅ ሀገራዊ ተልዕኮን እየተወጣ ላለ ተቋም ይህን ትልቅ ሀገራዊ ተልዕኮ በማሳካት ሂደት ውስጥ ትልቅ እንቅፋት የሆነውን ሙስናን ለመከላከል ትልቅ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ ስልጠናው እጅግ አስፋላጊ ነው። በተለይ የጥቅም ግጭት ለሙስና መንስኤ ስለሆነ በጥቅም ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሰጠቱ ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ በእጅጉ ይረዳል። አንዳንድ ጊዜ ባለማወቅ የጥቅም ግጭት የሚከሰትባቸው ውሳኔዎች ሊተላለፉ ይችላሉ። ስለሆነም የዚህ ሥልጠና ዋና ጥቅሙ የጥቅም ግጭት መንስኤዎች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ማስተዳደር ይቻላል? መሬት ላይ ያለው ነባራዊ ሁኔታስ ምንድን ነው የሚለውን ለመለየት ትልቅ ግንዛቤ የሚፈጥር ስለሆነ ከከፍተኛ አመራሩ በጥንቃቄና በጥብቅ ዲሲፕሊን ውሳኔዎችን እንዲያሳልፍ ይረዳዋል።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የጥቅም ግጭትን ለመከላከል እና ለማስተዳደር የሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ የሚያስፈልግበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ፡- እንደሚታወቀው ሥነምግባር የሁሉም ነገር መሰረት ነው። የጥቅም ግጭት ብዙ ጊዜ ውሳኔ ሰጪው አካል ላይ የሚወድቅ ነገር ነው። የመወሰን ፈቃደ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሀላፊነቱን ሲወጣ የህዝብ ጥቅም ከግል ጥቅም ሳይጋጭበት መወሰን የሚችለው ሥነ-ምግባራዊ ሲሆን ብቻ ነው። ሥነ-ምግባርን የተላበሰ አመራር የተሰጠውን ሀላፊነት ግልፅነት እና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ፍትሐዊ፣ ተገቢ እና ሚዛናዊ ለማድረግ አይቸገርም። አንድ ሰው ሙያው የሚጠይቀውን ሥነምግባራዊ እሴት ካላከበረ ለጥቅም ግጭት መጋለጡ አይቀርም። ለጥቅም ግጭት መጋለጡ ብቻ ሳይሆን ችግሩ ሲያጋጥም መከላከልም ሆነ ማስተዳደር አይችልም። የጥቅም ግጭትን ደግሞ ማስተዳደር ካልቻለ ወደ ሙስና የመቀየር እድሉ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊነት ዋነኛ ምክንያት አጣብቂኝ ውሳኔዎች ሲያጋጥሙ ችግሮቹን ከብዙ አቅጣጫ በማየት መፍታት ስለሚያስችል ነው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የጥቅም ግጭት በመከላከል እና በማስተዳደር ረገድ የዘርፉ ከፍተኛ አመራር ሚና ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?

ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ፡- አንደኛ ስለጉዳዩ በቂ ግንዛቤ መያዝ ተገቢ ነው። ምክንያቱም የጥቅም ግጭትን መከላከልም ሆነ ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ መወሰን የሚቻለው የጥቅም ግጭት ባህርይውን እና መንስኤውን መረዳት ሲቻል ነው። ሁለተኛ ለጥቅም ግጭት ተጋላጭ የሆኑ የሥጋት አካባቢዎችን በመለየት ሙስና እንዳይፈፀም ክፍተቶችን በአሰራር መዝጋት ነው። ሶሥተኛው ከተቋሙ የስራ ባህርይ አንፃር ውሳኔዎች ተለዋዋጭና አስቸኳይ ሊሆኑ ስለሚችሉ በዚህ ሂደት ውስጥ የጥቅም ግጭት ሊያጋጥም እንደሚችል በመረዳት ሙስና ከመሆናቸው በፊት አስቀድሞ መከላከል የሚያስችል የአስተዳደር ስልት መከተል ያስፈልጋል። አራተኛ ሰራዊቱ ሀገራዊ ግዳጁን በብቃት እና በጀግንነት እየተወጣ ባለበት ቁርጠኝነት እና ተነሳሽነት የእድገት እና የልማት ፀር የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሰራር አምርሮ በመታገል የዘርፉን የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ በላቀ ውጤት ማስቀጠል ነው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- እንደሚታወቀው ዘርፉ በፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ባስመዘገበው የላቀ አፈጻጸም በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና እና ሽልማት ማግኘቱ ይታወቃል። ይህንን ውጤታማነት ለማስቀጠል አመራሩ ለመከታተያ ክፍሉ ያለው ድጋፍ እና ተነሳሽነት ምን ይመስላል?

ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ- እንደተባለው በዘርፉ የተመዘገበው ጥሩ አፈጻጸም የመከታተያ ክፍሉ ትጋት እና የአመራሩ ቁርጠኝነት ታክሎበት የመጣ በመሆኑ ትልቅ ተነሳሽነትን ፈጥሯል። ይህን ውጤት ለማስቀጠል ከዋናው መ/ቤት ጀምሮ በተጠሪ ተቋማት ለሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በየደጃው ያለው አመራር ከፍተኛ ድጋፍ እና እገዛ እያደረገ ይገኛል። በየወሩ ግምገማዎች ይካሄዳሉ፣ ምን ጥንካሬ አለ፣ ምንስ ጉድለት አለ የሚለው እየተገመገመ ክፍተቶች ካሉ የሚታረሙበት አቅጣጫ እየተሰጠ ይገኛል። ስለሆነም አመራሩ በብዙ መልኩ ክፍሉን ለመደገፍ ከፍተኛ ፍላጎት አለው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ረገድ ከመከላከያ ዘርፍ ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ምን መሆን አለበት ብለው ያስባሉ?

ሌተናል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ፡- ኮሚሽኑ በተለይ በዚህ ሁለት አመታት በሥነ-ምግባር ግንባታ ዙሪያ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ነው። እኛ ለምንጠይቃቸው ሙያዊ እገዛዎች አሰልጣኝ ከመላክ ጀምሮ የሚያደርገው ድጋፍ እንዳለ ሆኖ በተለይ እኔ የማደንቀው በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ እየሰራ ያለውን ስራ ነው። በሚዲያ ስርጭታችሁ አንድም ቀን የግንዛቤ መልዕክት ሳይለጠፍ ውሎ አያውቅም። እኛም እየተከታተልን ለተቋማችን ማህበረሰብ ተደራሽ እያደረግን እንገኛለን። ስለዚህ ይህ ቅንጅታዊ አሰራር የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ነው ያለበት።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በመጨረሻም ቀረ የሚሉት ወይም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

ሌተንል ኮሎኔል ዘለቀ ረጋሳ፡- በሥልጠናው በርካታ የመከላከያ አመራሮች የታደሙበት እና ትልቅ ግንዛቤ የተፈጠረበት ብዙ ልምድ ያገኘንበት ነው። ዋናው እና ትልቁ ነገር የሥነ-ምግባር ግንባታው ስለሆነ ኮሚሽኑ በዚህ ላይ እየሰራ ያለውን ተግባር አጠናክሮ ይቀጥል እላለሁ።

ሳይቃጠል በቅጠል

ሙስና የአገርን ኢኮኖሚ መሠረታዊ በሆነ መንገድ የሚያናጋ በመሆኑ የሁሉም ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ያስፈልጋል!

ሙስና ከሥነ-ምግባር ጉድለት ባለፈ የአገርን የኢኮኖሚ ሕይወት መሠረታዊ በሆነ መንገድ የሚያናጋ ሲሆን፣ በተለይም ድብቅ ታክስ (Hidden Tax) ተብሎ መገለጹ እጅግ ትክክለኛ እይታ ነው። ማንኛውም የቢዝነስ ተቋም በሕጋዊ መንገድ ለመንግሥት ከሚከፍለው ግብር በተጨማሪ በጉቦ መልክ የሚጠየቀው ክፍያ የምርት/ንግድ ወጪውን (Production Cost) በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚጨምርበት፣ ይህ ወጪ በመጨረሻ በሸማቹ ሕዝብ ኪስ ላይ በማረፍ የኑሮ ውድነትን ያስከትላል።

በኢኮኖሚክስ ዕይታ "ኪራይ ሰብሳቢነት" (Rent-seeking) የሚባለው ሂደት ሰዎች አዲስ እሴት ከመፍጠር ወይም ፋብሪካ ከመገንባት ይልቅ፣ ባለው ሀብት ላይ ተጽዕኖ በመፍጠርና ጉቦ በመውሰድ ትርፍ ለማግኘት የሚጥሩበት አጥፊ መንገድ ነው። በዚህም ምክንያት ሀብት ከአምራቾች (Producers) ወደማያመርቱ ግን ሥልጣን ወዳላቸው ሰዎች ስለሚፈስ፣ የአገር አጠቃላይ ምርት እንዲቀንስና የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲገታ ያደርጋል።

በሙስና ምክንያት የሚገነቡ መንገዶች፣ ድልድዮችና ሕንፃዎች ያሉ መሠረተ ልማቶች ጥራታቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው ለሕዝብ ደኅንነት አደጋ ከመሆኑም በላይ ግዙፍ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራን ያስከትላል። ለምሳሌ ያህል አንድ መንገድ ለአሥር ዓመት እንዲያገለግል ታቅዶ በሙስና ምክንያት ጥራቱ ጎድሎ በሁለት ዓመት ውስጥ ቢፈርስ፣ መንግሥት ለጥገና የሚያወጣው ተጨማሪ ገንዘብ ለሌላ ልማት መዋል የነበረበትን ሀብት ያባክናል፤ ይህም በኢኮኖሚክስ የዕድል ወጪ (Opportunity Cost) ተብሎ የሚጠራው ትልቅ ኪሳራ ነው። ከዚህም ባለፈ በሙስና የተገኘ ገንዘብ "ምንጩ ምንድነው?" የሚል ጥያቄን በመፍራት በአገር ውስጥ ኢንቨስት ከመደረግ ይልቅ ወደ ውጭ አገር ባንኮች ወይም ንብረቶች የሚሸሽበት የካፒታል ሽሽት (Capital Flight) ይፈጠራል። ይህ ድርጊት አገሪቱ ለልማት የሚሆናትን የውጭ ምንዛሬና የካፒታል ክምችት እንድታጣ በማድረግ የኢኮኖሚ አቅሟን ያደክማል።

የሙስና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በገበያ ውድድር ላይ ብቃት ያለው ሳይሆን ጉቦ የሚሰጥ እንዲያሸንፍ በማድረግ የገበያ መዛባትንና የዋጋ መወደድን የሚፈጥር ሲሆን፣ የሥራ ማስጀመሪያ ወጪን በመጨመር የውጭ ኢንቨስተሮች እንዲሸሹ ያደርጋል። በበጀት ረገድም ለጤናና ለትምህርት የሚሆን ገንዘብ እንዲዘረፍ በማድረግ የሰው ኃይል ልማት እንዲዳከም የሚያደርግ ሲሆን፣ በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ሕግ ለገንዘብ ባለቤቶች እንዲያደላ በማድረግ የንብረት ባለቤትነት መብትን ያናጋል።

ሙስናን ለመዋጋት እንደ ሲንጋፖር ያሉ አገሮች የተከተሉት የባለሥልጣናትን ደመወዝ የመጨመርና በሙስና የተገኘን ጥቅም የሚያሳጣ ከባድ ቅጣት የመጣል "ዜሮ ትዕግሥት" ሞዴል እጅግ ውጤታማ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።

ሙስናን ለመቀነስ የዲጂታል አገልግሎቶችን በማስፋፋት ከሰው ጋር ያለውን ንክኪ መቀነስ፣ የሕግ የበላይነትን በማጠናከር በሙሰኞች ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድና የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች ኑሯቸውን እንዲችሉ የደመወዝ ማሻሻያ ማድረግ ወሳኝ መፍትሔዎች ናቸው።

በተለይ የዲጂታል ክፍያና የኦንላይን አገልግሎቶች ግልጽነትን በመፍጠር ለጉቦ ያላቸውን ተጋላጭነት በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳሉ። የአገር ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው ሙስናን እንደ ድብቅ ታክስ በማየትና ሥርዓታዊ የሆኑ የመከላከያ መንገዶችን በመዘርጋት የአገርን ሀብት ለታለመለት የልማት ዓላማ ማዋል ሲቻል ብቻ ነው።

"ሙስና ድብቅ ታክስ ነው፤ ምክንያቱም በጉቦ መልክ የሚጠየቀው ክፍያ የንግድ ወጪን ስለሚጨምርና ይህም በመጨረሻ በሸማቹ ሕዝብ ኪስ ላይ ስለሚያርፍ ነው" ሲሉ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፕሬዝደንት ዛዲግ አብርሃ ሀሳባቸውን በአፍሌክስ የፌስቡክ ገጽ አስፍረዋል።

ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

ይህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚያደረገው ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ በማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ወይም ለሌላ ሰው ያስገኘ ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሰት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ ወይም ከማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላት መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የምዳረግበት ነው፡፡

በዚህም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት በነዳጅ ስርጭት ሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ፍርድ ቤት የቀረቡ 14 ተጠርጣሪዎችን መዝገብ ተመልክቷል፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን 1ኛ ተጠርጣሪ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚን አቶ እስመለዓለም ምህረቱ፣ 2ኛ የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን የነዳጅ ዘርፍ ም/ዳይሬክተር ዲባራ ፉፋ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በየክፍለ ከተማው በንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ የነዳጅ ቁጥጥር ቡድን መሪና ባለሙያዎችን ጨምሮ አጠቃላይ 14 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሎ ፍርድ ቤት ማቅረቡ ተመላክቷል፡፡ በዚህም መርማሪ ፖሊስ የተጠረጠሩበትን ጉዳይ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አቅርቧል፡፡ተጠርጣሪዎቹ ተገቢ ያልሆነውጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ መንግስት በከፍተኛ ወጪ በድጎማ የሚያቀርበውን ነዳጅ ከመመሪያና ከደንብ ውጪ በማሰብ ነዳጁን ለማይመለከታቸው አካላት ያለአግባብ እንዲሰራጭ በማድረግ በመንግስት ላይ ጉዳት በማድረስ ሙስና ወንጀል መጠርጠራቸውን ጠቅሶ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አብራርቷል፡፡

መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹ በፌደራል የመንግስት ተቋማትና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተለያዩ ክ/ከተሞች በኃላፊነት ተመድበው በመስራት ላይ እያሉ መንግሥት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ወደ ሀገር የሚያስገባዉን ነዳጅ ከተለያዩ የነዳጅ አስመጪ ኩባንያዎች፣ ከአዲስ አበባ ውጪ ከሚገኙ የክልል ነዳጅ ማደያ ባለቤቶችና የመንግሥት የስራ ሀላፊዎች እና ህገ ወጥ ደላሎች ጋር በጥቅም በመመሳጠር ለታለመለት ዓለማ እንዳይዉል አድርገዋል በማለት የጥርጣሬ መነሻውን ለችሎቱ አስረድቷል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ሆን ብለው ነዳጅ የሚያጓጉዙ ቦቴ መኪናዎች ወደ ነዳጅ ማደያ ስፍራ ገብተዉ እንዳያራግፉና መንግሥት ታሪፍ እስከሚጨምር እንዲቆዩ በማድረግ በህገ ወጥ መንገድ ተመልሶ ከሀገር እንዲወጣ በማድረግ መንግሥት በቂ ነዳጅ ወደ ሀገር ውስጥ እያስገባ ባለበት ሁኔታ ሆን ብለዉ ሰው ሰራሽ እጥረት እንዲፈጠር በማድረጋቸዉ በደረሰው ጥቆማ መነሻ በቁጥጥር ስር አውሎ በማጣራት ላይ እንደሚገኝ ለችሎቱ አስታውቋል፡፡ መርማሪ ፖሊስ 1ኛ ተጠርጣሪ እስመዓለም ምህረቱን በሚመለከት የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆነዉ በመስራት ላይ እያሉ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋሉ ግለሰቦች ጋር በመቀናጀት ከኩባንያዎች እና ማደያዎች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር የነዳጅ ምርት ከተባለው መዳረሻ ውጭ በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ እንዲወጣና በኮንትሮባንድ መንገድ እንዲሸጥ ማድረጋቸውን ጠቅሷል፡፡ በዚህም በሐምሌ ወር 2017 ዓ.ም ብቻ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ነዳጅ የጫኑ 68 ቦቴዎች (33 በኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት እና 35 በግል ኩባንያዎች የተጫኑ) እንዲሰወሩ አድርጓል የሚል የጥርጣሬ መነሻውን ለችሎቱ አስረድቷል፡፡ 2ኛ ተጠርጣሪ ዲባራ ፉፋን በሚመለከት ደግሞ የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን የነዳጅ ዘርፍ ም/ዳይሬክተር ሆነዉ በመስራት ላይ እያሉ ኃላፊነቱን ሽፋን በማድረግ በኢንቨስትመንት ሽፋን በቀጥታ ተጠቃሚነት ተመዝግበው ነዳጅ ለሚሰጣቸውና ኢንቨስትመንታቸው ለተቋረጠ፣ ፈቃድ ያልወሰዱ እና ስራ ያጠናቀቁ 800 የሚሆኑ አካላት ነዳጅ ያለገደብ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል የሚል የጥርጣሬ መነሻውን ለችሎቱ አቅርቧል፡፡

በኮንትሮባንድ መንገድ ነዳጅ ጭነው ሲንቀሳቀሱ በፀጥታ አባላት የተያዙ ቦቴዎችን የህጋዊነት ደብዳቤ ሽፋን በመስጠት እንዲለቀቁ አድርጓል በማለት ለችሎቱ የምርመራ መነሻውን ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አብራርቷል፡፡

በተጨማሪም መንግሥት ግንባታቸው ለተጠናቀቁ የነዳጅ ማደያ ፈቃድ መስጠቱን እንደሸፋን በመጠቀም አዲስ ለሚከፍቱ የማደያ አገልግሎት እኛ ነን ያስፈፀምነው በሚል እስከ 5 ሚሊየን ብር ድረስ በመቀበል ፍቃድ እንዲያገኙ አድርጓል፡፡መርማሪ ፖሊስ ከተራ ቁጥር 3 እስከ 14ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተጠርጣሪዎችን በተመለከት ተጠርጣሪዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ክ/ከተሞች ንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ ተመድበው ሲሰሩ የነዳጅ ምርት ለተጠቃሚው በህጋዊና በዲጂታል አሰራር መሸጡን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነቱን በመተው ከነዳጅ ማደያዎች ጋር የጥቅም ትስስር ፈጥረዉ የነዳጅ ምርት በህገ ወጥ መንገድ ከቦታ ወደ ቦታ እንዲዘዋወርና በኮንትሮባንድ እንዲሸጥ በማመቻቸት ለድርጊቱ ፈጻሚዎች ሽፋን ይሰጣሉ የሚል የሙስና ወንጀል የጥርጣሬ መነሻውን ለችሎቱ ገልጿል፡፡

መርማሪ ፖሊስ የነዳጅ ዋጋ ይጨምራል በሚል ወር በገባ ከ24 ጀምሮ ምርት የሚሰውሩና በኮንትሮባንድ የሚሸጡ ማደያዎች በህግ እንዳይጠየቁና ሰው ሰራሽ የምርት እጥረት እንዲከሰት እንደሚያደርጉ አመልክቷል፡፡ የነዳጅ ሽያጭ በህጋዊ የዲጂታል ፋይናንስ ስርዓት እንዳይፈጸም በማድረግ ከ 2 ነጥብ 6 ቢሊየን ብር በላይ የሚያወጣ ነዳጅ በኮንትሮባንድ እንዲሸጥ በማድረግ የነዳጅ እጥረት እንዲፈጠር፣ መንግሥት ገቢ እንዲያጣና የገንዘብ ዝውውሩ ከፋይናንስ ስርዓት ቁጥጥር ውጪ እንዲሆን ያደርጋሉ በማለት ለችሎቱ አብራርቷል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ ህገወጥ ሰርኩላር ደብዳቤዎችን በመፃፍ ከአዲስ አበባ ነዳጅ ጭነው ወደ ክፍለሀገር የሚሄዱ ከባድ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ እንዳይሸጥ በማድረግ መጉላላት እየፈጠሩ የሚገኙ መሆኑን ጠቅሶ ተጨማሪ የምርመራ ማጣሪያ ማከናወኛ የ14 ቀን ጊዜ ቀጠሮ እንዲፈቀድለት ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱን ጠይቋል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ በበኩላቸው ምንም አይነት ወንጀል አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው በመከራከር የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድላቸው የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱን ጠይቀዋል፡፡ የግራ ቀኝ ክርክሩን የተከታተለው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ፖሊስ ከጀመረው ምርመራ ስራ አንጻር ተጨማሪ ጊዜ ቀጠሮ መስጠት አስፈላጊነትን በማመን የ12 ቀን የምርመራ ማጣሪያ ጊዜ ለፖሊስ ፈቅዷል፡፡በተያያዘ መረጃ የቀድሞው የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኒኮላ ሳርኮዚ እ.ኤ.አ በ2007 ለተካሄደው የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ዘመቻ ከሊቢያ የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋል በሚል የተፈረደባቸውን ውሳኔ ለመቃወም ዳግም ፍርድ ቤት ቀረቡ፡፡ ሳርኮዚ የቀረበባቸውን ክስ በሙሉ የሚክዱ ቢሆንም፣ ባለፈው ዓመት ለተወሰኑ ቀናት በእስር ላይ ቆይተዋል፡፡ የፓሪስ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳግም ችሎት፣ የ71 ዓመቱን የቀድሞ መሪ የቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል ዕድል ይሰጣቸዋል ብሏል፡፡ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ከ2007 እስከ 2012 ፈረንሳይን ያስተዳደሩት እኒህ ቀኝ ዘመም ፖለቲከኛ፣ እ.ኤ.አ በ2021 ዝቅተኛው ፍርድ ቤት በወንጀል በማሴር ጥፋተኛ ብሏቸው የነበረ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት መታሰራቸው የመጀመሪያው የዘመናዊቷ ፈረንሳይ መሪ ሆነው ተመዝግበዋል፡፡ ባለፈው ጥቅምት ወር የፓሪስ እስር ቤት ገብተው ለ20 ቀናት ከቆዩ በኋላ መለቀቃቸው ይታወሳል፡፡ ሳርኮዚ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ተከታታይ የሕግ ፈተናዎች የገጠሟቸው ሲሆን፤ በሌሎች ሁለት ጉዳዮች ላይም የመጨረሻ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡ ሳርኮዚ እ.ኤ.አ በ2012 ለሁለተኛ ጊዜ ለመመረጥ ባደረጉትና ሳይሳካ በቀረው የምርጫ ዘመቻ ላይ ከገወጥ የገንዘብ ድጋፍ ተጠቅመዋል በሚል ተጨማሪ የእስራት ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ በአሁኑ የ"ሊቢያ ክስ" ሳርኮዚ የተላለፈባቸውን የአምስት ዓመት እስራት በመቃወም ይግባኝ ጠይቀዋል፡፡

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

ኪነ-ጥበብ

እንዲህ ነው ሲገለፅ

እንዲህ ነው ሲገለጽ ተግባርና ስራ፣
የመለዮው ትርጉም የሀገር አደራ፣
እንዲህ ነው ማሳያው የስብዕና ልኩ፣
አርዓያ ለትውልድ ያገር ባህል ወጉ፣
የሞራል ከፍታ መለኪያ ሚዛኑ፣
ሆኖ መገኘት ነው ታማኝ ለወገኑ።
ሙያውን አክባሪ ታማኝ ኩሩ ዜጋ፣
ጥቅም ሳያጓጓው ለሞራል የተጋ፤
ለማተብ ነው እንጅ አይኖርም ለስጋ።
ህዝብን ለማገልገል ዘወትር ሲታትር፣
ወድቆ ያገኘውን መልሶ በክብር፣
የሀቀኝነት ቃል ሆኖለት ምስክር።
ቀርፀው ያሳደጉት በምግባር ኮትኩተው፣
ለሀገር የሰጡት በእግራቸው ተክተው፣
መማርስ እንዲ ነው ማወቅ እስከ ጥጉ፣
ቃልኪዳን አክባሪ ታማኝ ለማዕረጉ።
ከዚህ ኩሩ ዜጋ የሀገር መከታ፣
መልካም ምግባር እንጅ ተንኮል የለው
ቦታ።